



አዲሲትዋ አክሱም ጽዮን

# ትንሣኤ



በ፲፬ኛው ምእት ዓመት የተሠራ
የመስቀል አይነት

www.ethiopianorthodox.org

# ታላቅ ምክር

ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን ።
ክፉውን ነገር ተጸየፉት ፤
ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ ፤
በወንድማማች መዋደድ ፤
እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ ፤
እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ ፤
ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ ፤
በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ ፤
ለጌታ ተገዙ ፤ (ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ፤)
በተስፋ ደስ ይበላችሁ ፤
በመከራ ታገሡ ፤
በጸሎት ጽኑ ፤
ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ ፤
እንግዶችን ለመቀበል ትጉ ።

ሮሜ ፲፪፡፱-፲፫

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ።
☎ 122033 ✉ 30750
አዲስ አበባ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org